Calgary
**Livery Transport Services**

## **መግለጫ #015**
## የሰው መጓጓዣ የንግድ መኪናዎችን በተመለከተ የወጣ የመመሪያ ንድፈ ሃሳብ ኣማራጮች
## የምክር ቤቱ ማሻሻያ

2020 ነሐሴ 7

---

በሐምሌ 28፡ 2020 የሰው ሙጓጓዣ የንግድ መኪናዎችን (ማለት ታክሲ፡ ሊሞዚን ወዘተ) በተመለከተ የወጣው ሪፖርት ለከተማው ምክር ቤት ቀርቦ ነበር።

ምክር ቤቱ የሚከተለውን ማሻሻያ አጽድቋል፡
[የምክር ቤቱ የስብሰባ  ዝርዝር ክፍል 7.4]

ሀ) አሁን ያለውን ቅይጥ ክፍት እና ዝግ የሰው መጓጓዣ የንግድ መኪናዎችን ቁጥር በተመለከተ ባለበት እንዲቀጥል፡

ለ) የታክሲ ፕሌት አሰጣጥን በተመለከተ የአስተዳደር ውጪን እና ምክር ቤቱን በዚ ጉዳይ ላይ ያለውን ስራ የሚያጎድሉ አማራጮችን በምርመራ ሂደት ማጥናት፡

ሐ) የታክሲ ኩባንያዎች ከመንገድ ላይ ታክሲ ጠርቶ የሚሰቀል ደንበኛን በታክሲው የሜትር ዋጋ ስሌት መሰረት ሳይሆን አስቀድሞ ዋጋ በመነጋገር ክፍያን የመወሰን አማራጭ እንዲጠቀሙ መፍቀድ፡
መ) ለታክሲ/ሊሞሲን አሽከርካሪዎች የተቀናጀ የመንጃ ፍቃድ (ላይሰንስ) እንዲጀመር እና የተለየ የትራንስፖርት ኔትዎርክ ካምፓኒ የመንጃ ፍቃድ (Transportation Network Company) ባለበት እንዲቀጥል ማድረግ፡
ረ) ዋና የምርመራ ባለስልጣን ሌላ ውሳኔ እስካልሰጠ ድረስ የሰው መጓጓዣ የንግድ መኪናዎች ዕድሜ ከበዛ 10 ዓመት እንዲሆን ማድረግ እና በየ 12 ወራት ደግሞ አንድ ግዜ ምርመራ እንዲያደርጉ ማድረግ፡
ሰ) የመኪና ምልክቶችን በተመለከተ ታክሲዎች የተሻለ አማራጮች እንዲኖራቸው ማድረግ፡ ይሁን እንጂ የደህንነትን የተደነገገ ደንብ እንዲያሟሉ እንዲሁም የሚታይ የኩባንያ ምልክት ብኋላ እና በፊት የመኪና መስታወት ላይ እንዲኖር ማድረግ፡
ሸ) ካሜራ ያለው የሰው መጓጓዣ የንግድ መኪና እየቀዳ ከሆነ ተሳፋሪው በግልጽ በሚያየው ቦታ ላይ በካሜራ እየተቀዳ እንደሆነ የሚያስረዳ ምልክት እንዲኖር መደንገግ፡
ቀ) የታክሲ ፕሌት ያላቸው ፕሌቱን የሚያከራዩቡትን ቋሚ ዋጋ እንዴት መወሰን እንደሚቻል ማጥናት፡

የሚከተሉት ሃሳቦች ጸድቀዋል፡
ምክር ቤቱ ለአስተዳደሩ የሚከተሉት መመሪያዎች አስተላልፏል፡

1. የሰው መጓጓዣ የንግድ ትራንስፖርት ሕግ ላይ ዘረኝነት የሚያወግዝ እና ጸረ-ዘረኝነትን የሚደግፍ ውስጠ ደንብ በመጨመር ያለውን ውስጠ ደንብ ማሻሻል፡ ይህ ደግሞ የሚከተሉትን እና ሌሎችን ያጠቃልላል፡
   ሀ) ኢንደርስትሪውን በሚመለከት
   ለ) የመኪና መንዳት ስልጠናን በሚመለከት
   ሐ) ተያያዥ የከተማ ፍቃድ መስጫ እና የአፈጻጸም ስራዎችን በሚመለከት
   መ) የግንኙነትና የግንዛቤ ሃሳቦችን በሚመለከት
2. ዘረኝነትን በተመለከተ የሚደረጉ ሃሳቦችን በኩባንያው ደረጃ ከሚካሄዱ የጸረ ዘረኝነት ስራዎች ጋር በውህደት ማካሄድ፡

ፊትን መሸፈንን በሚመለከት የወጣው ውስጠ ደንብ 28M2020፡ የሚከተሉትን ሃሳቦች አጽድቋል፡
[የምክር ቤቱ የስብሰባ ዝርዝር ክፍል 13.2]

የሰዎች መጓጓዣን በሚመለከት ያለው ውስጠ ደንድ 6M2007 እንዲሻሻል እና የሚከተሉት ሃሳቦች በ 86(b) (i.1)  ማለት ከንኡስ ክፍል 86(b) ቡኋላ በመጨመር፡ ከትራንስፖርት ኔትዎርክ አሽከርካሪ  ሌላ የመኪና አሽከርካሪ

(b) ሰውን መኪናው ላይ ላለመስቀል የሚችልበት ሁኔታዎች በሚለው ክፍል ላይ ይህ ቀጥሎ የተጻፈው ሃሳብ ተጨምሮበታል፡

> “(b.1) አንድ ሰው የፊት መሸፈኛ ጭንብል (ማስክ) ካላደረገ አሽከርካሪው ይህን ሰብ መኪናው ላይ ላለመስቀል ይችላል፡ ይህ ደግሞ ኮቪድ-19ን በተመለከተ በተደነገገው ግዜያዊ ውስጠ ደንብ 26M2020 ላይ ባለው መሰረት ነው። ይህ ግን በክፍል 4 ላይ የተጠቀሱትን የፊት መሸፈና ጭምብል (ማስክ) ከማድረግ ነጻ የሆኑትን ሰዎች አያካትትም”

**ቀጠይ እርምጃዎች፡**

- አስተዳደሩ ስለ የሰዎች መጓጓዣ የሆኑ የንግድ መኪናዎችን ላይ የወጣውን የማሻሻያ ውስጠ ደንብ በተመለከት በ2020 ከኢንዱስትሪው አካላት ጋር ውይይት ያደርጋል።

ሙሉውን ሪፖርት እዚህ ማግኘት ይቻላል፡ Livery Regulatory Framework Options, CPS2020-0708.

ምክር ቤቱ የተወያየበትን ሙሉ ሃሳብ እዚህ ማግኘት ይቻላል፡ July 27, 2020 Combined Meeting of Council Minutes

ይህ መግለጫ በአማርኛ፡ ሂንዲ፡ፑንጃቢ እና ኡርዱ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። በነዚህ ቋንቋዎች የተተረጎመውን ክፍል በዚህ ማግኘት ይቻላል፡ Taxi and limousine bulletins

ተጨማሪ ጥይቄ ካለ በዚ የኢሜል አድራሳ መጻፍ ይቻላል፡ ltsengagement@calgary.ca

በዚህ የሰዎች መጓጓዣ የንግድ መኪናዎችን በሚመለከት የወጣው ውስጠ ደንብ ላይ ተሳታፊ ስለሆኑ እናመሰግናለን።

ከሰላምታ ጋር



ኮሪ ፖርተር
የሰዎች መጓጓዣ የንግድ መኪናዎች ቤት ጽሕፈት ተጠባባቂ ሃላፊ
ካልጋሪ ኮሚኒቲ ስታንዳርድስ